ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ
Nib InternationalBank

ግንቦት 05 ቀን 2017 ዓ.ም

# የተከበራችሁ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ባለአክሲዮኖች

ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በተፃፈ ደብዳቤ አክሲዮኖችን ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በኤሌክትሮኒክስ ይዘት ለመመዝገብ ይቻል ዘንድ የባለአክሲዮኖችን መረጃ አዘጋጅተን እንድንልክ ተጠይቀን ባሳወቅናችሁ መሰረት የኢትዮጵያ ዲጂታል የመታወቂያ ካርድ (ፋይዳ) በማቅረብ ለዚሁ ዓላማ የተዘጋጀውን ቅፅ እየሞላችሁ ትገኛላችሁ፡፡ በቅርቡ ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተላከልን ቅፅ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ማቅረብ ለሁሉም ባለአክሲዮኖች አስገዳጅ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም፡-

1. ከዚህ ቀደም ባሳወቅነው መሰረት ፋይዳ መታወቂያ አቅርባችሁ የተዘጋጀውን ቅፅ የሞላችሁ ግለሰብ ባለአክሲዮኖች የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት (TIN) ኮፒ ብቻ ገቢ እንድታደርጉ፤

2. ከዚህ ቀደም ባሳወቅነው መሰረት ቀርባችሁ የተዘጋጀውን ቅፅ ያልሞላችሁ ግለሰብ ባለአክሲዮኖች ፋይዳ መታወቂያ ወይም ምዝገባ ስታከናውኑ በአጭር የፅሑፍ መልዕክት የተላከላችሁን ባለ 16 አኃዝ ቁጥሮችን፣ የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሂሳብ ቁጥራችሁን እና የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት (TIN) በመያዝ መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀውን ቅፅ እንድትሞሉ፤

3. ነዋሪነታችሁ በውጭ ሀገር የሆነና ፋይዳ መታወቂያ ማውጣት ያልቻላችሁ ኢትዮጵያውንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ግለሰብ ባለአክሲዮኖቻችን በፓስፖርት መስተናገድ እንደምትችሉ ስለተገለፀልን ፓስፖርት፣ የባለአክሲዮኑን የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ሂሳብ ቁጥር እና የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት (TIN) በማቅረብ በተወካያችሁ አማካኝነት ቅፁን እንድትሞሉ፤

4. ከዕድሮችና ማህበራት ውጪ በአድራሻችሁ ቅፅ ተልኮላችሁ ቅፁን ሞልታችሁ ያልመለሳችሁ ድርጅት ባለአክሲዮኖቻችን ቅፁን በመሙላት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፍኬት (TIN) ኮፒ አባሪ በማድረግ ገቢ እንድታደርጉ፤

5. ዕድሮችና ማህበራት ባለአክሲዮኖቻችን እናንተን በምን መልኩ ማስተናገድ እንዳለብን ከኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን መመሪያ እየጠበቅን በመሆኑና መመሪያው እንደደረሰን የምናሳውቃችሁ በመሆኑ በትዕግስት እንድትጠብቁን እንጠይቃለን፡፡

**ማሳሰቢያ**፡- ክቡራን ባለአክሲዮኖቻችን ምዝገባው ቶሎ መጠናቀቅ ያለበት በመሆኑ ከላይ የተጠየቁ መረጃዎችን በማሟላት እስከ ሰኔ 30 ቀን 2017 ዓ.ም በአቅራቢያችሁ በሚገኝ የባንካችን ቅርንጫፍ ወይም ዋናው መ/ቤት 1ኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የባለአክሲዮኖች አስተዳደር ዋና ክፍል በመቅረብ በተጠየቀው መሰረት አስፈላጊውን ሁሉ እንድታጠናቅቁ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡